# <u>የዓላማ ጽናት !</u>

ክንዴን ሳልንተራስ ፤ ሞቼ ሳልቀበር
እኔነቴ አክትሞ ፤ እስኪጫነኝ አፈር
ጠኋት ያነሳሁት ፤ የትግል መርሆዬ
ሆኖ ይመራኛል ፤ የትግል ፋናዬ
ለሀገር ለወገን ፤ ይዉላል ጊዜዬ
ፊቴን አላዞርም ፤ ሳይሰምር አላማዬ
ሁሌም ከጎንሽ ነኝ ፤ ኢትዮጵያዬ እምዬ ።

በዱር በገደሉ ፤ ታግለው የወደቁ
በከተማው ትግል ፤ በፋሽስት ያለቁ
ቃል ኪዳን አለብኝ ፤ የጓዶች አደራ
አላማቸው ሰምሮ ፤ ችቦውን ላበራ ።

እኔም እንዳለፉት ፤ ባላማ ጸንቼ
የፋሽስት ሰለባ ፤ በሆኑት ጓዶቼ
ትግሌን እገፉለሁ ፤ አርማውን አንስቼ ።

ትግሉም ይቀጥላል ፤ ማቸነፉን አውቆ
በአላማው ጸንቶ ፤ እምነቱን ሰንቆ
ከህዝብ ወግኖ ፤ ማተቡን ጠብቆ ።

ስልጣን የህዝብ ሆኖ ፤ መብቱ እስከሚከበር
ቃልኪዳን አለብኝ ፤ ጽኑ እማይበገር
ጠኋት የተከልኩት ፤ ችግኙ ሳይጸድቅ
አበባው አብቦ ፤ አረሙ ሳይወድቅ
እኔም ካላማዬ ፤ ወይ ፍንክች ፤ ወይ ንቅንቅ ።

አርሶ አደሩን ይገፔ ፤ ላብ አደሩን ይገፔ
በህብረ ብሄራዊ ፤ ደምቄ ታግገፔ
የህዝብን ጥያቄ ፤ ብሶት ተመርኩገፔ
ጋራ ሸንተረሩን ፤ ጫካውን ተጉገፔ
ጠላት እየቀላሁ ፤ ሳንጃዬን መዝገፔ
በድል አድራጊነት ፤ ትግሉ ይጠናቀቃል
ሥልጣን የህዝብ ሆኖ ፤ ተከብሮ ይጸድቃል
ህዝብ የበላይ ሆኖ ፤ ጸረ ህዝብ ይደቃል
ሰቆቃው መከራው ፤ ያን ጊዜ ያበቃል ።

ታዛቢው